## ዶ/ር ሥርግው ለኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት በኢትዮጵያ ያደረጉዋቸው አስተዋጽኦች።

ከዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ ጋር የተዋወቅሁት በ፲፱፻፶፯ ዓ. ም. በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በታሪክ መምህርነት እንደተቀጠርኩ ነበር። ለአስር ዓመታት ያህል አብሬያቸው ስሰራ አብዛኛው ጊዜ አንዷን ቢሮ በጋራ በመጠቀም ነበር። ላገራቸውና ኢንዲሁም ላገራቸው ባህልና ታሪክ በጣም ከፍተኛ ፍቅርና ቀናኢነት ስለነበራቸው ምሳሌያቸውን እንድከተል አድርገውኛል። የነበራቸውን ጥልቅ የኢትዮጵያ እውቀትና ወጣት ተማሪዎች ያገራቸውን ታሪክ በደንብ እንዲገነዘቡና እንዲያስከብሩ ያሳዩት የነበረውን ጥረታቸው በመመልከት ፈለጋቸውን ለመከተል ሞክሬያለሁ።

በዘመናዊ የትምህርት አሰጣጥ ስርዓት ዶ/ር ሥርግው የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የታሪክ ምሩቅ ነበሩ። በዚያን ጊዜ በኢትዮጵያ ባህልና ታሪክ ጥናትና ምርምር የሚያካሒዱት የውጭ አገር ሰዎች ብቻ ስለነበሩ በአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ የታሪክ ክፍል እንዲቋቋም ዋና ቀስቃሽ ሆኑ። በዩኒቨርስቲው ውስጥ በኃላፊነት ቦታ ከተቀመጡት ከዶ/ር አክሊሉ ሀብቴና ከዶ/ር ሙሊጌታ ወዳጅ ጋር ጥሩ የሀሳብ መግባባት ስለነበራቸው ኢትዮጵያዊያን በታሪክ መምህርነት እንዲቀጠሩ ወደ ውጭ አገር ተልከው በከፍተኛ ደረጃ እንዲሰለጥኑ በመገፋፋታቸው ለብዙዎቻችን መቀጠርና በከፍተኛ ደራጃ መመረቅ ምክንያት ሆነዋል።

ዶ/ር ሥርግው በታሪክ መምህርነት ሥራቸውን ሲጀምሩ በአንደኛና በሁለተኛ ደራጃ ት/ቤቶች የታሪክ ትምህርት ቢሰጥም የአፍሪካንና የኢትዮጵያን ታሪክ አይጨምርም ነበር። የጥንቱ የግብጽና የባቢሎንያ፣ የግሪክና የሮም፣ ያአውሮጳ፣ የአሜሪካና የአስያ ታሪክ ባጠቃላይ፣ ከዚህም አልፎ የአውስትራሊያና የፖሊኒዚያ ታሪክ በሥርዐተ ትምህርቱ ሲካተቱ የአፍሪካና የኢትዮጵያ ታሪክ አይነካም፣ አይነሳም ነበር። የሁለተኛ ደራጃ መልቀቂያ የታሪክ ፈተናው የሚያዘጋጀው በክፍሉ ስለነበር የአፍሪካና የኢትዮጵያ ታሪክ በሁለተኛ ደረጃ ስርዐተ ትምህርት እንዲገባ ተከራክረዋል፣ ተሳክቶላቸዋልም።

ለሰፊው ሕዝብ በሚያመች ስልትና ቋንቋ የኢትዮጵያ ታሪክ ትምህርት በራዲዮና በጋዜጣ እንዲሰጥ በማሳሰባቸው ዋና ዋና ብሔራዊ በዓላት በሚከበሩባቸው ቀናት የታሪክ ክፍል በየተራ ትምህርትና መግለጫ መስጠት እንዲጀመር አስተዋጽኦ አድርገዋል።

ለዶክተርነት ማዕረግ የሚያበቃ የምርምር መጽሐፋቸው በጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ ሲሆን መጀመሪ በዩኒቨርስቲ ተማሪነት ቀጥሎ ደግሞ በመምህርነትና በመስክ ጥናት ያካበቱት እውቀት ሰፊና ጥልቅ ነበር። በርካታ የኢትዮጵያና የአውሮጳ ቋንቋዎችን በማወቃቸው ጽሑፎቻቸው ለተማሪዎችና ለተመራማሪዎች እጅግ በጣም ጥሩ አስፈላጊ ሆነዋል። አሁን በቀላሉ የማይገኙ በመሆናቸው እንደገና ለምን አይታተሙም ብለው የሚጠይቁ ብዙ ናቸው።

ታታሪ መምህርና የሚያስተምሩትን የሚወዱ ስለነበሩ እስከ አብዮቱ መባቻ ድረስ ተማሪዎቻቸውንና የሚፈልጉ መምህራንን በገና የእረፍት ሰሞን ይዘው በመሔድ በጎንደር፣ በአክሱም፣ በየሃ፣ በመጠራና፣ በአዱሊስ የመስክ ጥናት ያስጠኑ ነበር።

የጥንቱ የኢትዮጵያ ታሪክ በአርኪዮሎጂ ጥናትና ምርምር ካልተደገፈ ስፋትና ጥልቀት ሊኖረው አይችልም ብለው ስለነበር፤ ከመጀመሪያውኑ በታሪክ ክፍልና በጥንታዊ ቅርሶት አስተዳደር መስሪያ ቤት ቅርብ ግንኙነትና ትብብር እንዲፈጠር ጥረዋል። አልቀጠለም እንጂ በመተባበር ታሪክ የሚባል መጽሔት በጋራ ማሳተም ተጀምሮ ነበር።

በ፲፱፻፷፬ ዓ. ም. የታሪክ ክፍል ሊቀመንበርነት ሲረከቡ ወዲያውኑ ሁለት ተመራቂ ወጣቶችን በረዳት መምህርነት እንዲቀጠሩ ሲያደርጉ ዋናው ዓላማቸው የአርኪዮሎጂ ትምህርት በክፍሉ እንዲሰጥ ሆነ።

በኢትዮጵያ አርኪዮሎጂ እውቅና ያገኙ ምሁራንን ለመቅጠር ቢሞክሩም ዩኒቨርስቲው በሚከፍለው ደሞዝ የተገኙት አንድ ወጣትና ጀማሪ አርኪዮሎጂስት ሆኑ። ተስፋ ሳይቆርጡ ከፍተኛ ልምድ የነበራቸው ፈረንሳውያን አርኪዮሎጂስቶች በጥንታዊ ቅርሶች አስተዳደር መስሪያ ቤት ይሰሩ ስለነበር በክፍሉ እንዲያስተምሩ እንዲፈቀድ ከፍተኛ ጥረት አድርገዋል። በመጨረሻም ጥረታቸው ተሳካና ዩኒቨርስቲው ከእድገት በህብረት ዘመቻ በኋላ ሥራ ሲጀመር በኢትዮጵያ አርኬዎሎጂና ጥንታዊ የድንጋይ ጽሑፎችን በማንበብና በመተርጐም የታወቁ ፈረንሳውያን ሊቆቹ በማስተማር መሳተፍ ጀመሩ። ዶ/ር ሥርግው ባቀዱትና በተለሙት መሠረት ይኸውና አሁን የአዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ በድኅረ ምረቃ ደረጃ በአርኬዮሎጂ ትምህርት ስልጥና እየሰጠ ይገኛል።

ዶ/ር ሥርግው ስላበረከቱዋቸው የምርምር ጽሑፎችና የማስተማሪያ መጻሕፍት፣ እንዲሁም የብራና መጻሕፍት ደብዛቸው ከመጥፋቱ በፊት በፊልም ተቀርጸው እንዲቀመጡና፣ ለተመራማሪዎችና ለምሁራን በሚያመች ሁኔታ ተዘጋጅተው እንዲቀርቡ ያደረጉዋቸው አስተዋጽኦች በሌሎች ተነግሯል።

ባጠቃላይ ዶ/ር ሥርግው በዩኒቨርስቲ ደረጃ የመጀመሪያው ኢትዮጵያዊ የታሪክ መምህር ብቻ ስይሆኑ የታሪክ ክፍላቸው ኢትዮጵያዊ የሆነ ፈር እንዲይዝና ዓላማ እንዲኖረው በማድረጋቸው እኛ ተከትለን ማስተማር የጀመርነው እሳቸውን ታላቁ መምህር እያልን እናስታውሳቸዋለን።

ቸሩ እግዚአብሔር የዶ/ር ሥርግው ሐብለ ሥላሴን ነፍስ እንዲምር እለምናለሁ። ለቤተ ሰቦቻቸውም መጽናናትን እንዲሰጣቸው እጸልያለሁ።

ፕሮፌሰር መርዕድ ወልደ አረጋይ
አዲስ አበባ ዩኒቨርስቲ
የፕሮፌሰር ሥርግው ሐብለ ሥላሴ የሰማንያ ቀን መታሰቢያ
ቅድስት ሥላሴ ካቴድራል
አዲስ አበባ
መጋቢት ፳፯ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ. ም.